# የለየለት አምባገነናዊነትን በጋራና በጽናት መታገል አሁንም መስመራችን ነው።

ኢሕአዴግ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ጀምሮ ለአምስት አመታት ጠንካራ ተቃዋሚ እንዳይኖር ሲሰራ ሲደከመ የነበረ ድርጅት ነዉ። ሕዝብ በነጻነት ከመረጠ ምንም አይነት ድምጽ ማግኘት እንዳማይችል በመገንዘቡ፣ አባላትን በገንዘብ በመግዛት፣ በተቃዋሚዎች መካከል መከፋፈል እንዲፈጠር በማድረግ ፣ አፈናዉንና ወከባዉን ችለዉ ጠንከረዉ የወጡ ድርጅቶች በሚወጡበት ጊዜ ደግሞ መሪዎቻቸዉን በማሰርና አባላቶቻቸዉን በማንገላታት፣ ኢትዮጵያዉያንን በዘር በመከፋፈል፣ በስልጣን የሚቆይበት ሁኔታ ለማመቻቸት ሞክሯል። የኢትዮጵያ ህዝብ ቀና ብሎ እንዲሄድ ሳይሆን በፍርሃት ድባብ ዉስጥ እንዲቀመጥ አደርጓል።

በኢትዮጵያ አንድነት የጸናና የማያወላወል አቋም ያለዉና ስምንት ድርጅቶች ያቀፈዉ፣ የምንደግፈዉ መድረክ ከኢሕአዴግ የሚደርስበትን ከፍተኛ ወከባና እንግልት ተቋቁሞ፣ በጣም ከባድና አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ዉስጥ ከ489 ወረዳዎች ለፓርላማ የሚወዳደሩ እጩዉችንና ከአርባ ሺህ በላይ ታዛቢዎችን ማዘጋጀት ችሎ፣ በከተማና በገጠር በየክልሎቹ በርካታ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል።

የመድረክ ሕዝባዊ ድጋፍ ጠንካራ መሆኑን የተገነዘበዉ ሕወሃት/ኢሕአዴግ «ከ97 ምርጫ ተምሬያለሁ» በሚል ታዛቢዎችን በማባረርና በመደብደብ ፣ ኮሮጆውችን በመቀየር፣ በአለም መሳቂያ እስኪሆን ድረስ 99.7 % አሸንፌያለሁ ለማለት በቋቷል። መድረኩ ጠንካራ ተወዳዳሪ ሆኖ በመቅረቡ የኢሕአዴግ የዴሞክራሲ የዉሸት ካባ ሊገፈፍ ችሏል። አገዛዙን በገንዘብ የሚደግፉ የምእራባዉያን አገራት ሳይቀሩ ተቃዉሟቸዉን እንዲያሰሙ ተገደዋል።

የምርጫዉን ሂደትን በተመለከተ መድረክን የምንደግፍ በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዉያን የሚከተሉቱን አቋሞች በግልጽ እናስቀምጣለን፡

1. ህወሃት/ኢሕአዴግ 99.7 በመቶ የፓርላማ መቀመጫዎችን አሸንፌያለሁ ያለበት የዚህ የ2002 ምርጫ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲን ሂደት ሰላሳ አመት ወደ ኋላ እንዲመለስ ያደረገ፣ የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም አገዛዝ ያስታወሰን አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተት ነዉ። በመሆኑን አጥብቀን የምናወግዘዉ ሲሆን የሕወሃት/ኢሕአዴግን ሕጋዊነት በጭራሽ የማንቀበለዉ መሆናችንን እንገልጻለን። በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በጠመንጃ ጉልበት በኃይለ የተጫነ አገዛዝ እንደመሆኑን ለዚህ አፋኝ አገዛዝ መዉደቅ በቁርጠኝነትም እንታገላለን።

2. መድረኩ በቅርቡ ባወጣዉ መግለጫ ምርጫዉ እንደተጭበረበ የገልጸ ሲሆን የምርጫዉን መጭበርበር የሚያሳዩ መረጃዎችን ተንትኗል። በመሆኑም መድረኩ ይህንን ምርጫ እንደማይቀበለዉ በገሃድ አረጋግጧል። መድረኩ የወሰደዉ ትክክለኛ አቋም ያስደሰተንና ሙሉ በሙሉ የምንደግፈዉ መሆናችንን ለማረጋገጥ እንወዳለን።

3. መድረኩ በአገራች ያለዉን የተወሳሰበ የፖለቲካ ችግሮች በመፍታት ዙሪያ ያሳየው ብስለት ያለው አካሄድ የሁሉንም ኢትዮጲያኖች ስጋቶች አስወግዶ ለጋራ ድል በጋራ ህዝብን በማታገሉ ዛሬ በሚሊየኖች ደጋፊና አባላትን አሰባስባል። መድረክ የአቶ መለስን አስተዳደር ከመቀየር አለፎ በኢትዮጵያ በወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የሚታገል አካል ነዉ። መድረኩ ከተመሰረተ ረጅም ጊዜ የለዉም። በዚህ በአጭር ጊዜ ዉስጥ የሕህወት/ኢሕአዴግ ዘረኛ የከፋፍለህ ግዛን ፖለቲካ ያመከነ ሲሆን ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የሚደረገዉን ትግል በሁሉም የኣገሪቷ ክፍል ሁሉ፣ ዘርና ኀያማኖት ሳይለይ እየተቀጣጠለ ነዉ። የሕወሃት/ኢህአዴግ በትርና ዱላ በያቤሎ፣ በተንቤን፣ በደብረ ታቦር፣ በክብረ ነገስትና በሁሉም የአገሪቷ ክፍል ዜጎች ላይ ሁሉ አርፋል። አሁን ትግሉ ትግሬ ከአማራዉ ጋር፣ አሮሞው ከሶማሌዉ ጋር አይደለም። ትግሎ በኢትዮጵያ ህዝብና በመለስ ዜናዊ የሚመራዉ ጥቂት የማፊያ ቡድን ጋር ሆኗል። ይህም ለአገራችን ትልቅ ድል ነዉ እንላለን።

4. በዚህ በምርጫ ሂደት በቀዳሚነት ሰላባ የሆነቸዉ የምንወዳትና የምንኮራባት እህታችን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ናት። አቶ መለስ ከአሥራ ስምንት ወራት በፊት ርካሽና መሰረት በሌለዉ ምክንያት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወደ ቃሊቲ እንድትሄድ ያደረገዉ፣ የ2002 ምርጫ አጭበርብሮ ለማሸነፍ ከነበረዉ

ፍላጎት አንጻር ነዉ። አሁንም ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች የፓለቲካ እስረኞች በአስቸካይ እንዲፈቱ እየጠየቅን ለዚህም ጠንክረን እንደምነሰራ በድጋሜ ቃል እንገባለን።

5. ወከባዉና እንግልቱ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በማሰር ብቻ አላቆመም። በየክልሉ የአንድነት፣ የኦፍኮ እንዲሁም በርካታ የመድረኩ አባል ድርጅቶች ጽ/ቤቶች ተዘግተዋል። በርካታ የመድረኩ አባላት ተደብደበዋል። ከሥራ ተባረዋል። በትግራይ ወንድማችን አረጋዊ ገብረ ዮሀንስ፣ በኦሮሚያ ወንድማችን ቢያንሳ ዳባ ተሰዉተዋል። በምርጫዉ ሰሞንም በርካታ የመድረኩ ታዛቢዎች ድብደባና ከፍተኛ እንግልት የደረሰባቸዉ ሲሆን የሕወሃት የግፍ በትር በከፍተኛ ሁኔታ በመድረኩ ላይ ተዘርግቷል።

   በዉጭ አገር የምንኖር የመድረኩ ደጋፊዎች ሕይወታቸዉን እስከመስጠት፣ ወደ እሥር ቤት እስከ መዉረድ እንዲሁም የተለያዩ መከራዎች እስከመቀበል ለደረሱ ወገኖቻችን ያልንን አክብርትን ፍቅር መግልጽ እንወዳለን። ከነዚህ በአገር ቤት በእሳት ዉስጥ ትግል ለሚያደርጉ ጀግኖቻችን መቼም ቢሁን ያለንን ድጋፍ እናበዛዋለን እንጂ እንደማንቀንስ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

ዉድ የአገራችን ልጆች፣

ትግሉ በአራት ኪሎ በቤተ መንግስት መግባት አይደለም። ትግሉ በፓርላማ መቀመጫዎች መያዝ አይደለም። የትግሉ ዋና አላማ ኢትዮጵያን ማዳን ነዉ። የትግሉ ዋና አላማ ህዝቡ የአገሩ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ነዉ። የትግሉ አላማ ኢትዮጵያዊያንን ማሰባሰብና ማደራጀት ነዉ። ህዝቡ ሲደራጅን፣ ኢትዮጵያዉያን በአንድ ላይ ሲመጡ ያኔ ለአንባገነኖች ቦታ አይኖራቸዉ። በመሆኑ አገር ቤትና ከአገር ዉጭ ያለኸዉ ወገኖች ሁሉ ዘር ኃይማኖት ጾታ ሳይለየን በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዘን የአምባገነኖችን ስረአት በጋራና በጽናት እንድንታገል ጥሪ እናቀርባለን።

በአገር ቤት ለሚታገልዉ ወገናችን ያለን ድጋፍ ለመግለጽና ኢሕአዴግ ለሕዝብ ያለዉን ንቀት በመቃወም ከፍተኛ የተቃዉሞ ሰልፍ ከሌሎች ኢትዮጲያኖች ጋር በመተባበር በ ጁን 14 በዋሽንግተን ዲሲ ተተዘጋጅታል በዚህም የተቃውሞ ሰልፍ ላይ በመላው አሜሪካ የምትገኙ ኢትዮጲያዊያን በነቂስ በመውጣት ለወገኖቻችን ሰቆቃ ተግባራዊ ምላሽ እንድንሰጥ ህዝባዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ኢትዮጲያ ለዘላለም ትኑር

የሰሜን አሜሪካ አንድነት ድጋፍ ድርጅቶች ማህበር
የኦሮሞ ፌድራላዊ ኮንግረስ ድጋፍ ቡድን በአሜሪካ
የደቡብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ደጋፊዎች በሰሜን አሜሪካ
የአረና ትግራይ የድጋፍ ቡድን በአሜሪካ